የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 63
ADDIS ABABA 23rd May 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፴፯/፪ሺ፫
የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ ፭ሺ፰፻፸፪

CONTENTS

Regulation No.237/2011
Adama Science and Technology University
Establishment Council of Ministers Regulation
.................... ......................................... Page 5872

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፯/፪ሺ፫

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም
የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፯/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. **ዋና ግቢ**

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአዳማ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬. **የተሻረ ደንብ**

የአዳማ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳/፲፱፻፺፰ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 237/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF ADAMA SCIENCE AND TECHNOLOGY UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5 (1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the "Adama Science and Technology University Establishment Council of Ministers Regulation No. 237/ 2011"

2. ***Establishment***

1/ The Adama Science and Technology University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

3. ***Main Campus***

The University shall have its main campus at Adama and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. ***Repealed Regulation***

The Adama University Establishment Council of Ministers Regulation No. 120/2006 is hereby repealed.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

**፭. ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በደንብ ቁጥር ፩፻፳/፲፱፻፺፰ ተቋቁሞ የነበረው የአዳማ ዩኒቨርሲቲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለዩኒቨርሲቲው ተላልፈዋል፡፡

**፮. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**5. *Transfer of Rights and Obligations***

The rights and obligations of the Adama University established under Regulation No. 120/2006 are hereby transferred to the University.

**6. *Effective Date***

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of May, 2011.

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት